# 1. የማፍ ችሎታና ተፅዕኖ አድራጊ ተለውጦዎች ዝምድና፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በሁለተኛው "ሳይክል" በሚማሩ ተማሪዎች ተተኳሪነት[1]


**[1]ዶ/ር አሚ ሰውነት [2]ዶ/ር አለሚየሁ ተማስገን**

1. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ
2. የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ



***አህፅሮተ ጥናት***

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማበተማሪዎች የማፍ ችሎታና በነፃ ተለውጦዎች (በተማሪዎች ተነሳሽነት፣ በማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ በቤተሰብ ማገረታቻ፣ በቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ በቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ በተማሪዎች ፆታ፣ በተማሪዎች እድሜና በተማሪዎች የትውልድ ቦታ) ማካከል ያለውን ዝምድና ማለየት ሲሆን፣ ነፃ ተለውጦዎች ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና አላቸው? ከነፃ ተለውጦዎች ማካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸው የትኞቹ ናቸው? የሚሉ ሁለት ማሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመማለስ ሞክሯል፡፡ ጥያቄዎችን ለመማለስ፣ በጎዛምን ወረዳ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ "ሳይክል" ትምህርት ቤቶች በእጣ ንሞና የተመረጡ 265 ተማሪዎች በሚደጃ ምንጩነት አገልግለዋል፡፡ ሚደጃውን ለማሰብሰብ የማፍ ክሂል ፈተናና የፅሁፍ ማኪይቅ ጥቅምላይ ውለዋል፡፡ የተሰበሰበው ሚደጃ ሁለቱንምማሰረታዊ ጥያቄዎች ለመማለስ በድህረት ትንተና ተተንትኖ፣ ነፃ ተለውጦዎች ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ማከነኛ (.121) ተዛምዶ እንዳላቸው፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃና የትውልድ ቦታ እንደቅደም ተከተላቸው ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸው ተለውጦዎች እንደሆኑ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በማሳት፣ በዚህ ጥናት ያልተዳሰሱ ሌሎች የማፍ ክሂል ተፅእኖ አሳዳሪ ተለውጦዎችን ያካተተ ተጨማሪ ጥናት ቢደረግና ከክሂሉ ችሎታ ጋር ያላቸው ዝምድና ቢታወቅ፣ እንዲሁም መምህራን የማፍ ክሂልን ሲያስተምሩ ከከተማልጆች በበለጠለገጠር ልጆች ትኩረት ቢሰጡየሚሉ ምክረ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡*



***መፍቻ ቃላት* (Key Words):- *የማፍ ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ችሎታ፣ ነፃ ተለውጦዎች፣***


**መግቢያ**

**የጥናቱ ዳራ**

የመፃፍ ክሂል ዋና አላማ መልእክትን ካለምንም መስናክል ለአንባቢያን ማድረስ ነው፤ ይሁን እንጂ ክሂሉ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች በበለጠ የተወሳሰበና አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ፃህፍት ዘወትር የአንባቢያንን የችሎታ ደረጃ እያስታወሱ በአስተውሎት እንዲፅፉ ይጠይቃል (Javed፣ Juan and Nazli፣ 2013፤ Nacira፣ 2010፤ Styati፣ 2010)፡ ፡ በተጨማሪም፣ ስለፅሁፉ ምልኡነት፣ ስለአንባቢው ስሜት፣ እያንዳንዱ ዘውግ ስለሚጠይቀው ማስፈርት ማወቅ አለባቸው (Farooq፣ Uzair-ul-Hassan and Wahid፣ 2012)፡ ፡ እነ ዚህን ነገሮች ያልተገነ ዘቡ ፃህፍትና በአግባቡ ያልተማሩ ተማሪዎች በመፃፉበት ጊዜ የሚጥሯቸውችግሮች ብዙ ናቸው(Bilal, and et al. 2013፣ Farooq፣ Uzair-ul-Hassan and Wahid፣ 2012)፡ ፡ በማስኩ ሰፊ ጥናት ማድረግ የቻሉ ተመራማሪዎች፣ ስነልቦናዊ፣ ግንዛቤያዊና ስነልሳናዊ ችግሮች ብለውበሶስት ዋና ዋና ምድቦች ይከፍሏቸዋል (Fisher፣ 2012፤ Myhill and Fisher፣ 2010)፡ ፡ ስነልቦናዊ ችግሮች የፃህፍትን ዝንባሌ (ማለትምተነሳሽነት፣ አማላካከት፣ ፍላጎት፣ ወዘተ.) የሚማለከቱ ሲሆኑ፣ ግንዛቤያዊ ችግሮች ፃህፍት ስለመፃፍ የሚኖራቸውን እውቀት (የሃሳብ እጥረትንና የሃሳብ አደረጃጀትን) የሚማለከቱ ናቸው፡ ፡ ስነልሳናዊ ችግሮች ደግሞ፣ የፃህፍትን የቋንቋ አጠቃቀም ጥበባዊ እውቀት ይማለከታሉ፡ ፡

ከተመራማሪዎቹ ሃሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው፣ መልእክትን በፅሁፍ ማስተላለፍ ለሚፈልጉ ፃህፍት አዎንታዊ ዝንባሌ፣ ከፍ ያለ የመፃፍ ግንዛቤና የቋንቋ አጠቃቀም ጥበባዊ እውቀት ያስፈልጓቸዋል፡ ፡ በሌላ አገላለፅ፣ ፃህፍት ያለችግር መፃፍ እንዲችሉ፣ በመጀመሪያ ለመፃፍ የሚኖራቸው ዝንባሌ አዎንታዊ የሚሆንበትን መንገድ መፈለግ፣ ከዚያም የሚፅፉበትን ርእሰጉዳይ ማጤንና ውስብስብ የሆኑ ንኡሳን የመፃፍ ክሂሎችን (የአፃፃፍ ስልትን፣ የአረፍተነገር አወቃቀርን፣ የቃላት አጠቃቀምን፣ ስርአተነጥብን፣ ወዘተ) ማስብ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ እንዲህ ስለሆነም፣ ክሂሉ "እሳቤ ብዙና ክሂለ ብዙ ክሂል" እየተባለ ይታወቃል (Abu Shawish 2009፤ Moochi፣ 2013)፡ ፡

የመፃፍ ክሂል ችግሮች ብዛትና አለማቀፋዊነት ያላቸው፣ በየደረጃው በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ጎልተውየሚታዩ ናቸው (Chokwe፣ 2011)፡ ፡ በዚህ ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች በደረጃውመፃፍ ያለባቸውን ፅሁፍ መፃፍ አይችሉም(Lea and Street፣ 1998)፡ ፡ Munro (2003) በአለም አቀፍ ደረጃ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያደረጉት ጥናት እንደሚያስረዳው፣ የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ የደከመ ነው፡ ፡ ለድክመቱ በምክንያትነት ከሚገሱ ተላውጦዎች መካከል የተማሪዎች ተነሳሽነት ማጣት፣ የመምህራን ብቃት ማነስ፣ የሚፃፍበት ቋንቋ አፍ ያልተፈታበት (ሁለተኛ ቋንቋ) መሆንና ብቁ ያልሆኑ ማስተማርያ ዘዴዎችን

ማጠቀም እንደአብነት ተጠቅሰዋል (Chokwe 2011፤ Munro፣ 2003)፡፡ McGroarty (2009) በበኩላቸው፣ በማዳፍ ችሎታ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ተለውጦዎችን የተማሪዎች ማሳሳት፣ የመምህራን የማዳፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች የቀደመእውቀት፣ ፆታ፣ እድሜና የትውልድ ቦታ ብለውይከፍሏቸዋል፡፡

ከላይ ከቀረበውሃሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ተማሪዎች (በተለይም ጀማሪዎች) ሚልእክትን በፅሁፍ ማስተላለፍ እንዲችሉ አዎንታዊ ዝንባሌ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መምህራን ከሁሉ አስቀድመውተማሪዎች ለመዳፍ የሚኖራቸውዝንባሌ አዎንታዊ እንዲሆን መጣር አለባቸው፡ ምክንያቱም ለመዳፍ የሚኖራቸው ዝንባሌ አዎንታዊ ካልሆነ ተነሳሽነት አይኖራቸውም፤ ከደረጃቸውአንፃር ማከናወን የሚገባቸውን የመዳፍ ክሂል ተግባራትምማከናወን አይችሉም፡

አንድ ተማሪ ውጤታማ በሆነ ስልት ወይም ዘዴ ትምህርቱ ካልቀረበለት በስተቀር አዎንታዊ አመለካከት ወይምተነሳሽነት ስላለውብቻምውጤታማሊሆን አይችልም፡ ከስነዘዴውበተጨማሪ በተወለደበት ቦታ፣ በሚማርበት የክፍል ደረጃ፣ በእድሜ፣ በፆታ፣ በጓደኞቹ፣ በመምህሮቹና በወላጆቹ የተነሳ ተፅዕኖ ሊደርስበት ይችላል፡፡ McGroarty (2009) Baker (1992)ን በመጥቀስ፣ ፆታ፣ የቋንቋ ዳራ፣ ባህልና ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በሚማሩት በመዳፍ ክሂል ብሎምበቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ያስረዳሉ፡፡

Ellis (1999) Labov (1991)ን በመጥቀስ እንደሚሉት፣ አንድ በተረጋጋ ወይም ቋሚ በሆነ ማህበረልሳናዊ የቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ኢመደበኛ የሆነ ውን የቋንቋ አጠቃቀም ይጠቀማሉ፡፡ በሌላ አባባል ሴቶች ከወንዶች የበለጠ መደበኛ የሆነውን ወይም ተቀባይነት ያለውን አጠቃቀምይጠቀማሉ፡፡ Finlay (2004) ይህን ሃሳብ ሲያረጋግጡ፣ የሴቶችና የወንዶች አእምሮ አካላዊ ልዩነት አለው፤ ውስጠ ጆሮ አሰራሩ፣ አወቃቀሩና የማነረታዊ ነርቮች አቀማመጥ የተለያየ ነው፤ ይህ አእምሯዊ ልዩነትም ለተለያዩ የትምህርት አይነቶች የተለያየ የግንዛቤ ደረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ተመራማሪው አያይዘውም የሴቶች አእምሮ ለቋንቋ የወንዶች ለሳይንስ ትምህርቶች እንደተፈጠረ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት፣ ተማሪዎችን በፆታ ከፋፍሎ ማስተማር እንደሚበጅ የሚመክሩ ተመራማሪዎች ጥቂት አይደሉም (Adeyemi፣ 2008፤ Chase፣ 2011፤ Moochi፣ 2013)፡፡

ሌላው ተማሪዎች በሚፅፉበት ጊዜ ለሚሰሯቸው ስህተቶች በሰበብነት የሚጠቀሰው ጉዳይ፣ ተለምዷዊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ጥቅምላይ ማዋል ነው(Adas and Bakir ፣ 2013፤ Nacira ፣ 2010)፡ ፡ ተለምዷዊ ዘዴ በየደረጃው ባሉ የክፍል ደረጃዎች ቋንቋን ለማስተማር በጣም ተዘውትሮ የሚሰራበት ዘዴ ነው፡ ፡ መጀመሪያ አስተማሪው ፅንሰሃሳቦችን፣ እውነታን፣ እንዲሁምሂደቶችን ያስተምራል፤ ከዚያምተማሪዎች በተማሩት ማሰረት እውቀታቸውንና ሂደቱን በማጠቀም ችግር እንዲፈቱ ይደረጋል፡ ፡ የራሳቸውን ብልሃት ፈጥረው እንዲማሩ እድል አይሰጥም፤ አማራጩቸው ለማምህሩ ጥገኛ መሆን ነው(Kilpartrick፣ 1985)፡ ፡ ይህ አይነቱ ዘዴ ተማሪዎች በራሳቸውእውቀት፣ ተሞክሮና መንገድ ለችግሮች መፍትሄ እንዲፈልጉ አያበረታታም፡ ፡ በጥገኝነት መኖርን ወይም ተስፋ ቆርጦ መቆምን የሚያስከትል ነው፡ ፡ በተጨማሪም፡ ተማሪዎች ወደፊት በህይወት ለሚገ ጥሟቸውችግሮች ሁሉ መፍትሄ ሊሆን አይችልም(Carpenter and Lehrer፣ 1999)፡ ፡ ስለሆነም፡ ተማሪዎች ሲማሩ አዳዲስ ክሂሎችንና እውቀቶችን እንዲፈጥሩ ጠቃሚበሆኑ ዘዴዎች ትምህርቱን ማቅረብና በዚያውም ችግር ፈቺነትን ማለማመድ ይገባል (Mochesela et al፣ 2007)፡ ፡

ከላይ ከቀረበውሃሳብየምንረዳው፣ በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ የተለያዩ ተፅዕኖ አድራጊ ተላውጦዎች መኖራቸውን ነው፡ ፡ በMcGroarty (2009) እሳቤም፡ በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ለመሆንምላለመሆንምተጠያቂ የሆነ አንድተላውጦየለም፡ ፡

**1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር**

ብዙ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ በየደረጃውያሉ ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነት የላቸውም (Cliff and Hanslo፣ 2009፤ Granville and Dison፣ 2009)፡ ፡ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች ደግሞበየደረጃውየሚሰጡትን የመፃፍ ክሂል ተግባራት መወጣት አይችሉም(Cliff and Hanslo፣ 2009)፡ ፡ Niven (2005) እንደሚሉት፣ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች ሲፅፉ በሚፈፅሙት ችግርና በየደረጃውበሚጠበቀውፅሁፍ መካከለል ሰፊ ልዩነት አለ፡ ፡ ይህ ማለት በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው እንዲፅፉ የሚጠበቅባቸውን ፅሁፍ መፃፍ አይችሉም፡ ፡ ምክንያቱም፡ ወደየክፍል ደረጃውየሚገቡ ተማሪዎች በደረጃውእንዲፅፉ ለሚጠበቀውፅሁፍ ብቁ ሆነውና ተነሳሽነት ኖሯቸውየሚማጡአይደሉም(Hirst et al.፣ 2004)፡ ፡

በመፃፍ ክሂል ትምህርት የመምህራን የብቃት ውስንነትምችግር ይፈጥራል (Chokwe፣ 2011)፡ ፡ በተለምዶ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተነሳሽነት አለመኖር ከተማሪዎች ብቻ የሚመነጭ ተደርጎ ይገመት ነበር፤ መምህራን በሃሳቡ ባይስማሙም Moore (1998) እና Moutlana (2007)

እንደሚሉት፣ የተማሪዎች የመፃፍ ችግር መምህራን በሚኖራቸው የብቃት ውስንነት ሊፈጠር ይችላል፡፡ መምህራን የመፃፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ጊዜ የራሳቸውንና የተማሪዎቻቸውን ችግሮች በየጊዜው እየፈተሹ መፍትሄ ሚሊለግ ይጠበቅባቸዋል (Niven፣ 2005)፡፡ "ጥሩ መምህር ያስተምራል፤ በጣም ጥሩው ያብራራል፤ እጅግ በጣም ጥሩው ያነሳሳል" (Zhu፣ 2004) እንዲሉ፣ የመፃፍ ክሂል መምህራን ተቀዳሚተግባር፣ ተማሪዎቹን ማነሳሳትና ችግራቸውን መፍታት ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲያውም ቋንቋን (በተለይም መፃፍን) ማስተማር አይቻልም፤ የሚቻለው የመማሪያ ሁኔታዎችን (መማሪያ ዘዴዎችን) ማመቻቸትና ተማሪዎችን ማነሳሳት ነው (Adas and Bakir፣ 2013፤ Bilal et al፣ 2013)፡፡

በመፃፍ ብሎምበቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ፆታምትኩረት ሊሰጠውይገባል፡፡ ምክንያቱም፣ ባደጉ ሃገራት የተሰሩት ፍትነታዊ (Experimental) ጥናቶች፣ ወንድና ሴት ተማሪዎች፣ የመፃፍን ክሂል ጨምሮ ማንኛውንምየቋንቋ ትምህርት በጋራ ሲማሩ፣ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ተጠቃሚእንደሆኑ አረጋግጠዋል (Adeyemi፣ 2008፤ Chase፣ 2011፤ Moochi፣ 2013)፡፡ በሃገር ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶችን ስንመለከት ግን፣ በውጭሃገር ከተካሄዱት የጥናት ውጤቶች ጋር የሚቃረኑ ናቸው፡፡ ይኸውም፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ችሎታና በፆታ ልዩነት ለሁለተኛና ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተደረጉ ሶስት ጥናቶች የተለያዩ ውጤቶችን አሳይተዋል፡፡ ለምሳሌ ፋንቱ (1989 አ.ም) በ11ኛ ክፍል ባደረጉት ጥናት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የቋንቋ ችሎታ ልዩነት እንደሌለ ሲያሳዩ፣ ጌታቸው (2001 አ.ም) በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች፣ አማረ (2009 አ.ም) በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ባደረጓቸውጥናቶች ወንድ ተማሪዎች ከሴት የክፍል አቻዎቻቸውበተሻለ መፃፍ እንደሚችሉ አሳይተዋል፡፡

የቤተሰብ የኑሮ ደረጃና የቋንቋ ችሎታም አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው፡፡ McGroarty (2009) Burstall (1975)ን በመጥቀስ እንዳቀረቡት፣ የዝቅተኛው መደብ አባል የሆኑ ተማሪዎች በትምህርታቸው የከፍተኛው መደብ አባል ከሆኑ ተማሪዎች ያነሰ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በእርግጥ የተማሪዎች ማህበራዊ ደረጃ ከተለያዩ የኢኮኖሚደረጃና ብሄር በማጡተማሪዎች ላይ ከተግባቦታዊ ቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥና መናገር) አንፃር በችሎታቸው ላይ ምንም ልዩነት አላመጣም፡፡ ከመደበኛ የቋንቋ ትምህርት አንፃር ግን መካከለኛ ገቢ ያላቸው ተማሪዎች የሰራተኛውመደብአባል ከሆኑ ተማሪዎች የበለጠችሎታ አሳይተዋል፡፡

ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለመፃፍ ክሂል፣ ተማሪዎች ተነሳሽነትና ክህሎት የላቸውም፡ ለምን? የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ ብዙ ሚለሶችን ማስጠት ቢቻልም፣ የማስተማሪያ ዘዴ አማራረጥና

አተገባበር ችግር ቀዳሚ ቱን ሊወስድ ይችላል፡፡ ሚረው (1996 ዓ.ም) እንደሚሉት፣ የመፃፍ ክሂልን አዋጪበሆነ ዘዴ አለማስተማርና በአብዛኛው በንድፈ ሃሳብ ወይም በይዘት ላይ ብቻ አተኩሮ ማስተማር አሚርኛ ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችግር ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ Clouthier and Shandola (1993) በበኩላቸው፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲያስተምሩ የንድፈሃሳብ ጥገኞች መሆን የለባቸውም ሲሉ፣ Cumming (2003) እና Hyland (2003) ደግሞ የመፃፍ ትምህርት ንድፈሃሳቦችን በማቅረብ ብቻ የሚያስተምሩት አለመሆኑን ያስረዳሉ፡፡ መሞር አዳዲስ ሃሳቦችን ከማግኘት በላይ ነው፤ ቅድመእውቀትን እንደገና ማንባትን ወይም ማደስን ይፈልጋል (Mochesela፣ 2007)፡፡ እንደክኒን የሚዋጥም አይደለም፤ ተማሪዎች በማህራቸው አማቻችነት እውቀቶችን የሚቀስሙት ወይም እንደገና የሚያደራጁበት፣ ከባዶ አእምሮነት ወይምከተቀባይነት በንቃት የሚሳተፉበት (ማለትምበመወያየት፣ በማስማማት ወይም በመቃወምየሚማሩት) ነው (Mochesela፣ 2007)፡፡ ለዚህ ደግሞ ተስማሚማስተማሪያ ዘዴዎችን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ ከቀረቡት ጥናቶች እንደምንማለከተው፣ የተለያዩ ተላውጦዎችን በተናጠል ከማጥናት ውጭ በመፃፍ ክሂል ችሎታ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ተላውጦዎችን (የተማሪዎች የቀደመ እውቀት፣ አማለካከት፣ ማሳሳት፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የኑሮ ደረጃ፣ ማበረታቻ፣ የመምህራን ማስተማሪያ ዘዴ፣ ፆታና በታ) አንድ ላይ ካጡኑ በኋላ የበለጠ ተፅዕኖ (ዝምድና) ያለውን ተላውጦ ወይም ያላቸውን ተላውጦዎች በማለየት ለችግሩ መፍትሄ የሚሆኑ ሃሳቦች ያቀረቡ ጥናቶችን የዚህ ጥናት አከናዋኞች ባደረጉት ሰፊ ንባብ ማግኘት አልቻሉም፡፡ የነዚህን ተላውጦዎች ትስስር በጥናት አለሚረጋገጥ ክሂሉን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙችግሮችን ለይቶ ለመቅረፍ አያስችልም፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማበተማሪዎች የመፃፍ ችሎታና በነፃ ተላውጦዎች (በተማሪዎች ተነሳሽነት፣ በመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ በቤተሰብ ማበረታቻ፣ በቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ በቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ በተማሪዎች ፆታ፣ በተማሪዎች እድሜ፣ በተማሪዎች የትውልድ በታ) መካከል ያለውን ዝምድና ማለየት ሲሆን፣ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜ፣ የተማሪዎች የትውልድ በታ ከተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና እንዳላቸው መግለፅ፣

2. በጥያቄ ቁጥር "1" ከቀረቡት ነፃ ተላውጦዎች ማካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠአዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸውየትኞቹ እንደሆኑ ማለየት፣

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

የማፍ ክሂል በአንድ ቀን የሚዳብር ስላልሆነ ፣ በችግሮች ዙሪያ በየጊዜው መውያየት፣ ማጋገር፣ ምርምር ማካሄድ፣ አጫጭር ሴሚናሮችን ማቅረብ ወዘተ. ያስፈልጋል፡፡ በሚሆኑም፣ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- ለማምህራንና ለተማሪዎች ማፍን በመማር ማስተማር ሂደት ተፅዕኖ የሚያደርጉ ተላውጦዎችን በማለየት ይጠቁማል፡፡
- ለማምህራንና ለተማሪዎች በማፍ ችሎታ ላይ የትኞቹ ተላውጦዎች የበለጠ ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ ሚረጃ ይሰጣል፡፡
- ለሞርሃትምህርት ቀራጮች፣ ለመፅሃፍ አዘጋጆች፣ ባጠቃላይ ለትምህርት ባለሙያዎች ስነትምህርታዊ እገዛ ያደርጋል፡፡
- ከዚህ ጥናት ርዕሰጉዳይ ጋር በተያያዘ፣ በማስኩ ለሚደረጉ ምርምሮች ማሻ በሚሆን ያገለግላል፡፡

### 1.5. የቁልፍ ተላውጦዎች ሚያዊ ብያኔ

**የማፍ ተነሳሽነት (writing motivation)፡ -** ፃህፍት የማፍ ተግባርን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚኖራቸውን የራስ መተማመን፣ ፍላጎት፣ ማቃቃት፣ ወዘተ. የሚያነሳሳ ወይም የማዳድብና ከግለሰቦች ውስጣዊ ወይምውጫዊ ስሜት የሚመነጭግፊት ነው፡፡

**የ መፃ ፍ ክሂል ችሎታ (writing skill performance)፡** - አንድ ፅሁፍ ከሃሳብ አፍልቆት/ ከይዘት፣ ከሃሳብ አደረጃጀትና ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ተገቢነቱ የሚመዘንበትና የችሎታ ደረጃ የሚሰጥበት አቢይ ማስፈርት ነ ው ፡

**ነ ፃ ተለዋጮዎች፡** - በዚህ ጥናት የተማሪዎችን ተነ ሳሽነ ት፣ ፆታ፣ እድሜ የትውልድ ቦታ፣ የክፍል ደረጃ፣ የመምህራንን የመፃ ፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብን የኑሮ ደረጃ፣ የትምህርት ሁኔ ታና ማበረታቻ ይጠቃለከታል፡ ፡

**ጥገ ኛ ተለዋጮ** - በዚህ ጥናት ጥገ ኛ ተለዋጮ የሚለው ቃል የሚወክለው የተማሪዎችን የመፃ ፍ ክሂል ችሎታ ብቻ ነ ው ፡

## የ አጠናን ዘዴ

### 2.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የተማሪዎች ተነ ሳሽነ ት፣ ፆታ፣ የክፍል ደረጃ፣ የትውልድ ቦታ፣ የመምህራን የመፃ ፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔ ታ፣ የኑሮ ደረጃና ማበረታቻ ከተማሪዎች የመፃ ፍ ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና ይፈትሻል፡ ፡ ስለሆነ ም ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡ ፡

### 2.2. የ ጥና ቱ ተሳታፊዎች

የ ወረዳውትምህርት ፅፈትቤት ሃላፊ በሰጡት መረጃ መሰረት በጎ ዛምን ወረዳ 38 የ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገ ኛሉ፡ ፡ ከእነ ዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል በእጣ ንሞና ስልት አምስት የ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡ ፡ የእጣ ንሞና ስልት የተመረጠበት ምክንያት፣ አንደኛ በወረዳውለሚገ ኙ ትምህርት ቤቶች እኩል እድል ስለሚሰጥና የ ጥና ቱን ውጤት በወረዳው ውስጥ ለሚገ ኙ የ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል ትምህርት ቤቶች ለማጠቃለል ስለሚያስችል ነ ው ፡ ሁለተኛ የ ሚጠናውክሂል የ መፃ ፍ ክሂል ስለሆነ ፣ ከዚህ በላይ ትምህርት ቤቶችን መርጦ ማጥናት አስፈላጊነ ቱ ባይካድም በየ ትምህርት ቤቱ የ ሚገ ኙትን ተማሪዎች ድርሰት በተለያዩ ማስፈርቶች ሚ ምግን ጊዜ የ ሚፈልግ በመሆኑ ነ ው ፡

በአምስቱ ትምህርት ቤቶች ከሚገ ኙት "ሳይክሎች" መካከል ደግሞ ሁለተኛው "ሳይክል" የ ሚከተሉትን ምክንያቶች ማስፈሪያ አድርጎ ተመርጧል፡ ፡

አንደኛ፣ በ"ሳይክሉ" ከሚማሩ ተማሪዎች የ ሚገ ኘው የ መፃ ፍ ችሎታ ውጤት በተመሳሳይ የ ክፍል ደረጃ አመርኛን ለሚማሩ አፍፈት ተማሪዎችና ለሚቀጥለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ መጀመሪያ "ሳይክል" ጠቃሚመረጃ ስለሚሰጥ ነ ው ፡

ሁለተኛ፣ ከዚህ በኋላ ለሚቀጥሉት የክፍል ደረጃዎች ማለትም ተማሪዎች ወደፊት ለሚገሩቸው የማፍ ችሎታ ማስረት የሚጥሉባቸው ወሳኝ የክፍል ደረጃዎች በመሆናቸው በማፍ ችሎታቸው ላይ ለሚታዩ ችግሮች ምንጭ የሆኑ ተለውጦዎችን ከወዲሁ አውቆ መፍትሄ መፈለግ ስለሚያስችል በታለሚንሞና ተመርጧል፡፡

Tabachnick & Fidell (1996)፣ በአንድ ጥናት የሚጠቀመው የናሙና ብዛት (No) > 50 + 8m (m የነፃ ተለውጦ ብዛት) መሆን አለበት፤ በሚሉት ማስረት፣ በዚህ ጥናት ለናሙናነት የተመረጡት ተሳታፊ ተማሪዎች ብዛት የኮክራንስን የናሙና ማጠን ቀመር (Cochran's Sample Size Formula) በማጠቀም265 እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ቀመሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

$$No = \frac{Z^2 P*Q}{D^2}$$

Where, No. = የተፈለገው የናሙና ማጠን፣ Z = በ95 እርግጠኛነት የZ ዋጋ 1.96 ተደርጎ ይወሰዳል፤

P (maximum variability) = በታለሚው አካላይ ውስጥ የሚገፈው ባህርይ ሲሆን ከዚህ በፊት የማይታወቅ ከሆነ በተለምዶ 0.5 ተደርጎ ተወስዷል፤

Q = 1-P ነው፡

D (Precision) = የስህተት ይሁንታ ማጠን ሲሆን በተለምዶ 0.05 ተደርጎ ተወስዷል፤ ከላይ የቀረበውን የስርጭት ቀመር በማያዝ አንድ ቁጥሩ ከታወቀ የጥናት አካላይ ውስጥ ወካይ የሆነ ናሙና ለመውሰድ የሚከተለውን ቀመር ማጠቀምተገቢ ነው፡

$$n = \frac{no.N}{N+(no-1)}$$

n = የናሙና ማጠን፣ no = ከላይ የቀረበውቋሚቀመር ሲሆን 384 ተደርጎ ተወስዷል፡፡

N = የጥናቱ አካላይ ማጠን ነው፡

ስለሆነም፡ የዚህ ጥናት የጥናት አካላይ (N) = 853 ሲሆን፣ የናሙናውማጠን እንደሚከተለው ተሰልቶ 265 ሆኗል፡፡

$$n = \frac{384 * 853}{853 + (384-1)} = \mathbf{265}$$

## 2.3. የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች የማፍ ክሂል ፈተናና የፅሁፍ ማጠይቅ ናቸው፡

### 2.3.1 የማፍ ክሂል ፈተና

የመፃፍ ክሂል ፈተናው ተማሪዎች በደረጃቸው ማወቅ የሚገባቸውን ክህሎት በተመለከተ ያሉበትን ደረጃ ለሚፈተሽ የሚያስችል ሲሆን የሚከተሉትን ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

1. አንደኛ የርእስ አመራረጥ፡- ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን ልምድና የክፍል ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለድርሰት መፃፊያ የሚሆኑ 10 ርእሶች በጥናቱ ተመራማሪዎች ከተመረጡ በኋላ ድርሰት በሚያስተምሩ መምህራን ተገምግመው ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ የሆኑ ሶስት ርእሶች ብቻ ቀርበውላቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ከእነዚህ ርእሶች አንዱን በመምረጥ ሶስት አንቀፅ ያለው አንድ ድርሰት እንዲፅፉ ተጠይቀው ፅፈዋል፡፡
2. ድርሰቱን የሚፅፉበት ቦታ፣ ጊዜና የቃላት መጠን፡- የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማወቅ የተዘጋጀውን የመፃፍ ክሂል ፈተና የትምህርት ቤቱን ርእሰ መምህርና የየክፍሎችን መምህራን በማስፈቀድ ትምህርት ቤት ውስጥ አጥኚዎች ባሉበት በመደበኛው መርሃግብር እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ተማሪዎች በተቃራኒ ፈረቃ እንዲመጡ ቢደረግ ለፈተናው ትኩረት ስለማይሰጡና ሁሉም ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች ሊገኙ ስለማይችሉ ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል ፈተናው በአንድ ሰዓት ውስጥ ከግማሽ እስከ አንድ ገፅ ወይም ከ150-200 በሚደርሱ ቃላት ከቀረቡላቸው ሶስት ርእሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ አንድ ድርሰት በነፃነት እንዲፅፉ ተደርጓል፡፡
3. የመፃፍ ክሂል ፈተና አዘገጃጀት፡- በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መፅሀፉ መሰረት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የሃሳብ አንድነት አጠባበቅ፣ የሃሳብ አደረጃጀት፣ ወዘተ. ስህተቶች ለማግኘት አስችሏል፡፡
4. የፈተናው አስተራረም፡- በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች የፃፏቸው የመፃፍ ክሂል ፈተናዎች በአንድ ቅጂ ተባዝተው በሁለቱ አጥኚዎች ታርመዋል፡፡ ፈተናዎቹ በሚታረሙበት ጊዜ (አባሪ "ለ" ይመለከቷል) ተመሳሳይ የሆነ የውጤት አሰጣጥ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይኸውም በአራሚዎች መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለማጥበብና ተመሳሳይ የአስተራረም ስልት ለማስፈን ይቻል ዘንድ የድርሰት አስተራረም መመሪያው ተባዝቶ ሁለቱም አራሚዎች ተጠቅመውበታል፡፡ በጠቃላይ በዚህ ጥናት “ተንታኝ” ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም፣ ተንታኝ የመፃፍ ክሂል ማረሚያ ዘዴ የመፃፍ ፈተናውን አስተማማኝነትና ተጨባጭነት ከፍ ያደርጋል (Weir፣ 1990)፡፡

### 2.3.2. የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት የፅሁፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ስለመፃፍ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የትውልድ ቦታ፣ የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታና የቤተሰብ የኑሮ

ሁኔታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዘምዶ ማሳየት ነው፡ በሚሆኑም እነ ዚህን ዓላማዎች ታሳቢ ያደረጉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ቀርበውላቸዋል፡፡ ጥያቄዎቹ ዝግና ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ዝግ ጥያቄዎችምበሊከርት ወይምበሬቲንግ ስኬል ሜልክ ቀርበዋል፡፡

ማጠይቁ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን፣ በክፍል አንድ አጠቃላይ የተማሪዎች ሚረጃ (ማለትም የክፍል ደረጃ፣ እድሜ ፆታ፣ የትውልድ ቦታ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ ማበረታቻና የቤተሰብየኑሮ ሁኔታ) ቀርቧል፡፡ የክፍል ደረጃውበሌላ ነገር ሳይወከል እንዳለ (5፣ 6፣ 7፣ 8 ተብሎ) የቀረበ ሲሆን፣ ፆታ የወንዶች በ"0" የሴቶች በ"1" ተወክሎ ቀርቧል፡፡ እድሜን አስሜልክቶ ከ12 አሜት በታች ያሉት በ"1" ከ12-15 በ"2" ከ15 በላይ ያሉት ደግሞበ"3" እንዲወከሉ ተደርገዋል፡፡ የትውልድ ቦታን በተማለከተ ገጠር በ"1" ከተማ በ"0" ሲወከል፣ የቤተሰብ መሜር አለመሜር የተሚረ በ"0" ያልተሚረ በ"1" ተወክሏል፡፡ የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ የተሻለ በ"0"፣ ማካከለኛ በ"1"፣ ዝቅተኛ በ"2" ተወክሏል፡፡ የቤተሰብ ማበረታቻን በተማለከተ ደግሞየሚያበረታታ በ"0" ሲወከል የማያበረታታ በ"1" ተወክሎቀርቧል፡፡ በክፍል ሁለት ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተነሳሽነትና የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ጥያቄዎች በአዎንታዊና በአሉታዊ መንገድ ቀርበዋል፡፡ ሁለቱም የቀረቡት በባለ አምስት ሊከርት ስኬል ሲሆን በቅደም ተከተል በጣም እስማማለሁ (5)፣ እስማማለሁ (4)፣ በማጠኑ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም(2)፣ በጣምአልስማማም(1) ነጥብ እንዲይዙ ተደርገዋል፡፡

## 2.4. የሚረጃ ማሰብሰቢያ ማሳሪያዎች አስተማማኝነት

Cohen (2000) "አስተማማኝነትንና ትክክለኛነትን የሚቃንሱ ነገሮችን ሜሉ በሜሉ ማጥፋት ይቻላል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው"፤ ይላሉ፡፡ ሜሉ በሜሉ መቆጣጠር ባይቻልም ምሁራን የሚያቀርቧቸውን ዘዴዎች ተግባራዊ በማድረግ መቀነስ ግን ይቻላል፡፡ በሚሆኑም የፅሁፍ ማጠይቅ ጥያቄዎችን አስተማማኝነት በተማለከተ በማስኩ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ማጠይቁን እንዲያዩትና ሃሳባቸውን እንዲሰጡበት በማጠየቅ፣ ከሜለሾች የተገኘውን ሚረጃ ማሳረት በማድረግ ሜጨምር የሚኖርባቸውጥያቄዎች ካሉ አዘጋጅቶ ሜጨምር፣ ማሻሻል ያለባቸው ካሉ ማሻሻል፣ መቅረት ያለባቸውን ማስወጣት፣ ግልፅነት የጎደላቸውን ማብራራት፣ ወዘተ. የሜለሾችን ሚረጃ ማሳረት በማድረግምየማጠይቆችን አስተማማኝነት፣ ከተቻለምትክክለኛነት መወሰን እንደሚገባ ያስገነዝባሉ (Muijs፣ 2004፤ ያለው፣ 1998 አ.ም)፡፡ በሚሆኑም የጥያቄዎችን አስተማማኝነት ለማወቅ 'ክሮንባክ አልፋ' ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም "ለሜለሾች የተሰጧቸው አማራጮች በሊከርት ወይም በሬቲንግ ስኬል ሜልክ ከሆነ 'ክሮንባክ አልፋ' ዘዴዎች ተማራጭ ት ይኖራቸዋል" (ያለው፣ 1998፣ 220)፡፡

ከማፍ ክሂሉ ፈተና የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝነት በተማለከተ ደግሞ የአራሚዎች አስተማማኝነት (Inter-rator Reliability) የክሮንባክ አልፋ ቀመርን በማጠቀም ተሰርቷል፡፡ ይኸውም ያለው(1998 አ.ም.) እና Cohen (2000) እንደሚሉት፣ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ዳኞች አንድን ባህሪ በተለያዩ ሰዎች ላይ ተሚለክተውእንዲገመገማ ተመሳሰይነቱን እንዲያማለክቱ ቢደረግ እነ ዚያ ዳኞች የተማለከቱትን ነገር ምን ያህል በተማሳሰይ ሁኔታ ለማማ ምችለዋል የሚለውን የሚያሳይ ነው፡ በአራሚዎች መካከል ያለው አስተማማኝነትም $\alpha$= .83 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህምተቀባይነት አግኝቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

## 2.5 የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት

ትክክለኛነት የምርምር ትክክለኛነት (Research Validity) እና የማለኪያ ትክክለኛነት (Measurement Validity) ተብሎ በሁለት ይከፈላል (Dornyei፣ 2007)፡፡

### 2.5.1 የምርምር ትክክለኛነት

የምርምር ትክክለኛነት እንደገና ውስጣዊና ውጫዊ ትክክለኛነት (Internal and External Validity) ተብሎ ይከፈላል፡፡ ውስጣዊ ትክክለኛነት ማለት በምርምሩ የተገኘውውጤት በጥናቱ ውስጥ በተጨመሩት ወይምቁጥጥር ላይ በዋሉት ተላውጦዎች ምክንያት እንጂ በሌሎች ተላውጦዎች ምክንያት አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡ ውጫዊ ትክክለኛነት ደግሞየምርምሩን ግኝት ለሰፊው የጥናቱ አካላይ (Population) ማጠቃለላችንን የሚያማለክት ነው(Dornyei፣ 2007፣ 46)፡፡

በመሆኑም የዚህን ጥናት ውስጣዊ ትክክለኛነት ከፍ ለማድረግ ከነፃ ተለዋዋጮች (ተማሪዎች ለማፍ ክሂል ካላቸውተነሳሽነት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ ከትውልድ ቦታ፣ መምህራን ክሂሉን ከሚያስተምሩበት ዘዴ፣ ከቤተሰብ ማገረታቻ፣ ከቤተሰብ የትምህርት ሁኔታና ከቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ) እና ከጥገኛ ተላውጦ (ከተማሪዎች የማፍ ክሂል ችሎታ) ውጬያሉትን ይህ ጥናት አልተማለከተም፡ Robson (1993) እንደሚሉት፣ መረጣ፣ መቼት (Setting)፣ ታሪክ፣ የተጠኚዎች ልዩ ባህርይ (Particular Constructs) በአንድ ምርምር ውጫዊ ትክክለኛነት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ናቸው፡ ከዚህ አንፃር የዚህን ጥናት ውጫዊ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፡ -

ሀ. ከተጠኚዎች አመራረጥ አንፃር፡ - Dornyei (2007) እና Singh (2006) እንደሚሉት፣ ወካይ ናሙና መምረጥያስፈልጋል፡፡ ይኸውምብዙ ናሙና ከወሰድን የአካላዩን (Population) ባህርይ የበለጠየሚወክል በመሆኑ በቀመሩ ማሰረት ወካይ ናሙና ተመርጧል፡፡

ለ. ከተጠኚዎች ልዩ ባህርይና ከሜቼት (setting) አንፃር፡- Marczyk et al. (2005) እንደሚያስረዱት ተጠኚዎች በባህርይ፣ በሜቼት (Setting) ወዘተ. ከሚበኛው ባህርያቸው የተለየ ሁኔታ የሚያሳዩ ከሆነ የምርምሩን ውጨዊ ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ ይከቱታል፡፡ ለዚህምሲባል፣ ለተማሪዎች የተሰጡት የማፍ ክሂል ፈተናና የፅሁፍ ማጠይቅ በተማሳሰይ ጊዜ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 2.5.2 የማእኪያ ትክክለኛነት

የማእኪያ ትክክለኛነት ደግሞ በተለያዩ ተላውጦዎች ማካከል ያለን ዝምድና የሚያማእክተውን ማስፈርት ተኮር ትክክለኛነት (Criterion Validity)፣ በፈተና የተገኘው ውጤት በንድፈሃሳብ ካለውጋር ያለውን ስምምነት የሚያማእክተውን ትወራ ተኮር ትክክለኛነት (Construct Validity) እና የይዘት ትክክለኛነት (Content Validity) የያዘ ነው(Dornyei፣ 2007)፡፡

በዚህ ማሰረት የፅሁፍ ማጠይቁንምሆነ የማፍ ፈተናውን የይዘት ትክክለኛነት Cohen (2000)፣ Mujis (2004) እና Weir (1990) እንደሚሉት፣ የፈተናውን ይዘት በባለሙያዎች በማስገምገም የሁሉምጥያቄዎች ወካይና ጠቃሚሚሆን ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥያቄዎቹን ግልፅነት ለማወቅ የዋናው ጥናት ሚረጃ ከማሳብሰቡ በፊት ተማሳሰይ የክፍል ደረጃ ባላቸው ሌሎች ተማሪዎች ላይ ቅድመ ጥናት (Pilot test) ተካሂዷል፡፡ በሚጨረሻም የተገኙ ተሞክሮዎችን በማከተት ዋናውጥናት ተከናውኗል፡፡

### 2.6. የሚረጃ ሙተንተኛ ስልቶች

በዚህ ጥናት ከማፍ ክሂል ፈተናና ከፅሁፍ ማጠይቅ የተገኙ ሚረጃዎች በአሃዛዊ የሚረጃ ሙተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ይኸውምየተማሪዎች የማፍ ክሂል ችሎታ በፈተና ተሰብስቧል፤ የተሰበሰበው ፈተና በሁለቱ አጥኚዎች (ባለሙያዎች) ታርሟል፡፡ በሚቀጠል በሁለቱ አራሚዎች ማካከል ያለው የአስተራረም ስምምነት በኮኸነስ ዲ የአስተማማኝነት ሚወሰኛ ዘዴ ተሰልቶ አስተማማኝ ሆኖ ስለተገኘ፣ የሁለቱ አራሚዎች አማካይ ውጤት ተወስዶ ለትንተና ውሏል፡፡ ከዚያም በተማሪዎች የማፍ ችሎታና በነፃ ተላውጦዎች ማካከል ያለው ዝምድና በድህረት ትንተና (Regression Analysis) ተሰርቷል፡፡ ድህረት ትንተና ያስፈለገበት ምክንያት፣ በአንድ ጥገኛ ተለዋዋጭ(የተማሪዎች የማፍ ችሎታ) እና ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነፃ ተለዋዋጮች (የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ ፆታ፣ እድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ የትውልድ በታ፣ የማምህራን የማፍ ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታና የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ) ማካከል የሚኖረውን ግንኙነት ለማሳየት ተሚራጭሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡ በጠቃላይ በዚህ ጥናት ማጠናዊ ስታቲስቲክስ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## 3. የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 3.1. የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ማሰረታዊ ጥያቄ፣ "የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማብረታታት፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና አላቸው?"፣ የሚል ነበር፡፡ ሚረጃው በማፍ ፈተናና በተነሳሽነት የፅሁፍ ማጠይቅ ተሰብስቦ፣ በድረት ትንተና ተተንትኖ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 3.1 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3.1. በነጻ ተለዉጦዎችና በመጻፍ ክሂል ችሎታ መካከል ያለዉ ዝምድና" በድህረት ትንተና

| **አር (R)** | **አር ስኩየር ($R^2$)** | **አጀስትድ አር ሰኩየር (Adjusted $R^2$)** |
|---|---|---|
| **.389** | .151 | .121 |

ከሰንጠረዡ መሚልከት እንደሚቻለው፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማብረታታት፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ያላቸውን ዝምድና ለማሳየት R= .389, $R^2$ = .151, Adj $R^2$ = .121 ሆኖ ይታያል፡፡ ከውጤቱ መሚለከት እንደሚቻለው፣ በአስተማማኝነት የማስላት አቅም ያለው Adj $R^2$ = .121 ነው፡፡ ይህም፣ ከላይ የቀረቡት ተለዉጦዎች የማፍ ክሂል ችሎታን ማጠነኛ በሚባል መንገድ የመተንበይ አቅም እንዳላቸው ያስረዳል፡፡ ምክንያቱም፣ በድህረት ትንተና ተዛምዶ ከ0-1 ባለው ስኬል የሚወሰን ሆኖ፣ <0.1 ደካማ የመተንበይ አቅም፣ ከ0.11 - .3 ማጠነኛ የመተንበይ አቅም ከ0.31 - 0.5 መካከለኛ የመተንበይ አቅም እና>0.5 ጠንካራ የመተንበይ አቅም የሚሉ ማለኪያዎች ይኖሩታል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት (.121) ከ0.11 – 0.3 ባለው ያረፈ ስለሆነ፣ ነፃ ተለዉጦዎቹ ማጠነኛ የመተንበይ አቅምእንዳላቸውሚረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛውየጥናቱ ማሰረታዊ ጥያቄ፣ "በማሰረታዊ ጥያቄ ቁጥር "1" ከቀረቡት ነፃ ተለዉጦዎች መካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠአዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸውየትኞቹ ናቸው?የሚል ሲሆን፣ ትንተናውእንደሚከተለውበሰንጠረዥ 3.2 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3.2 ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸው ተለዉጦዎች ልየታ በድህረት ትንተና

| ነፃ ተላውጦዎች | B | Beta | የጉልህነት ደረጃ (Sig.) |
|---|---|---|---|
| የክፍል ደረጃ | 1.189 | .248 | .001 |
| እድሜ | 1.049 | .120 | .104 |
| ፆታ | -.739 | -.068 | .277 |
| የትውልድ ቦታ | -2.159 | -.169 | .006 |
| የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ | 1.226 | .113 | .072 |
| የቤተሰብ ማበረታቻ | .631 | .045 | .476 |
| የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ | .202 | .021 | .731 |
| የተማሪዎች ተነሳሽነት | .937 | .089 | .214 |
| የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ | -.203 | -.022 | .759 |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው፣ በBeta ልኬት የክፍል ደረጃ .248፣ እድሜ .12፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ .113፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት .089፣ የቤተሰብ ማበረታቻ .045፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ .021፣ የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ -.022፣ ፆታ -.068 እና የትውልድ ቦታ -.169 ሆኖ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ያላቸውን አዎንታዊ ተዛምዶ ያሳያል፡፡ ይህ ምማለት የክፍል ደረጃ ሲጨምር የመፃፍ ክሂል ችሎታ አብሮ ይጨምራል፡፡ የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከከተማ ይልቅ ገጠር መሆን ለመፃፍ ችሎታ ዝቅተኛ (-.169) መሆን መንስኤ እንደሆነ ምያሳያል፡፡ በጉልህነት ማጠን ማላኪያው በ(Sig.)ም እነ ዚህ ሁለቱ ተላውጦዎች (የክፍል ደረጃና የትውልድ ቦታ) ጉልህ አስተዋፅኦ (>.01) ሲኖራቸው፣ ሌሎቹ ተላውጦዎች ጉልህ አስተዋፅኦ የላቸውም፡፡

### 3.2. የውጤት ማበራሪያ

የዚህ ጥናት የመጀመሪያውንኡስ አላማ "የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና እንዳላቸው ማወቅ" ሲሆን፣ ተላውጦዎቹ በድምር፣ ማጠነኛ የመተንበይ አቅም (Adj $R^2$ = .121) እንዳላቸው ሚረዳት ተችሏል፡፡ ይህም፣ McGroarty (2009)፣ የተማሪዎች መነሳሳት፣ የመማህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ ፆታ፣ እድሜና የትውልድ ቦታ በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ተላውጦዎች ናቸው፣ ከሚሉት ሃሳብ ጋር በማጠኑ ይስማማል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ፣ በክሂሉ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ (በዚህ ጥናት ያልተዳሰሱ) ሌሎች ተላውጦዎች እንዳሉ ያማላክታል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ንኡስ አላማ "በመጀመሪያው አላማ ከቀረቡት ነፃ ተላውጦዎች ማካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸውየትኞቹ እንደሆኑ ማለየት ነበር፡፡ ይህን ለማለየት በተደረገውትንተና ከተላውጦዎች ማካከል የክፍል ደረጃና የትውልድ ቦታ በማፍ ክሂል ችሎታ ላይ ጉልህ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ (<.01 እንደሆኑ) ሚረጋገጥ ሲቻል፣ ሌሎቹ ተላውጦዎች ጉልህ ተፅእኖ እንደሌላቸው (>.01 እንደሆኑ) ሚረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም Gomathi (2014) ከገጠር የመጡተማሪዎች ከከተማእንደመጡት ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ማሪያዎች አይሟሉላቸውም፡ እናም እንደከተማ አደግ ተማሪዎች ለትምህርት አይነ ቃቁም፤ ከሚሉት ሃሳብ ጋር ሲስማማ ሌሎቹ ተላውጦዎች ከፍተኛ ተፅእኖ እንዳላቸው ከሚያስረዱት ከ McGroarty (2009) እና ከሌሎች ሃሳቦች ጋር ብዙምአይጣጣማም፡

## 4 ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና ምክረ-ሃሳብ

### 4.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተማሪዎች የማፍ ችሎታና በተፅዕኖ አሳዳሪ ተላውጦዎች ማካከል ያለውን ዝምድና ማለየት ሲሆን፣ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ እንዲማለሱ የተፈለጉት ማሳረታዊ ጥያቄዎችምየሚከተሉት ናቸው፡

1. የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና አላቸው?
2. በጥያቄ ቁጥር "1" ከቀረቡት ነፃ ተላውጦዎች ማካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠአዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸውየትኞቹ ናቸው?

እነዚህን ማሳረታዊ ጥያቄዎች ለመማለስ፣ ትምህርት ቤቶች በቀላል እጣ ንሞና፣ የክፍል ደረጃውበታላሚ ንሞና፣ ተማሪዎች በኮክራንስ የናሙና ማጠን ቀመር (Cochran's Sample Size Formula) ተመርጠዋል፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች ሚገኘው በማፍ ክሂል ችሎታ ፈተናና በፅሁፍ ማጠይቅ ተሰብስቦ በድህረት ትንተና ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም፡

አንደኛ፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብየትምህርት ሁኔታ፣ የቤተሰብየኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ምን አይነት ዝምድና አላቸው? ከሚለው ማሳረታዊ ጥያቄ ምላሽ፣ ማጠነኛ (.121) የሙትንበይ አቅም (ዝምድና) እንዳላቸው ሚዳት ተችሏል፡፡

ሁለተኛ፣ በጥያቄ ቁጥር "1" ከቀረቡት ነፃ ተለውጦዎች መካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ለሚለው ማሳረታዊ ጥያቄ ምላሽ፣ የክፍል ደረጃና የትውልድ ቦታ በማፍ ክሂል ችሎታ ላይ ጉልህ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ (<.01 እንደሆኑ) ሚረጋገጥ ሲቻል፣ ሌሎቹ ተለውጦዎች ጉልህ ተፅእኖ እንደሌላቸው (>.01 እንደሆኑ) ሚረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የክፍል ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የተማሪዎች የማፍ ችሎታ አብሮ ሊጨምር እንደሚችል፤ ከከተማ ልጆች ይልቅ የገጠር ተማሪዎች የማፍ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሚሆን አሳይቷል፡፡

### 4.2. መደምደሚያ

ከትንተናው ውጤት በመነሳት ይህን ጥናት እንደሚከተለው መደምደም ተችሏል፡፡

1. የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የክፍል ደረጃ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ማጠነኛ (.121) ተዛምዶ እንዳላቸው በጥናቱ ውጤት ሚረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ማለት ከነዚህ ተለውጦዎች በበዛ ለማፍ ችሎታ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ሎሎች ተለውጦዎች እንዳሉ ያማላክታል፡፡
2. በቁጥር አንድ ከቀረቡት ነፃ ተለውጦዎች መካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊና አሉታዊ ዝምድና ያላቸው የክፍል ደረጃና የትውልድ ቦታ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ማለት፣ የክፍል ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የተማሪዎች የማፍ ችሎታ አብሮ ሊጨምር እንደሚችል፤ ከከተማልጆች ይልቅ የገጠር ተማሪዎች የማፍ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም የክፍል ደረጃ ሚጨምር ለማፍ ክሂል ችሎታ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ሲኖረው፣ ገጠር መወለድ በበኩሉ ለማፍ ክሂል ያለው አስተዋፅኦ አሉታዊ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

### 4.3. ምክረ-ሃሳብ

ከጥናቱ ከተገኙት ውጤቶች (መደምደሚያዎች) በመነሳት የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች ማሳንዘር ተችሏል፡፡

1. የተማሪዎች ተነሳሽነት፣ የማፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ የቤተሰብ የትምህርት ሁኔታ፣ የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ የተማሪዎች ፆታ፣ የተማሪዎች እድሜና የተማሪዎች የትውልድ ቦታ ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር ማጠነኛ (.121) ተዛምዶ ብቻ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይህም፣ ከነዚህ ተለውጦዎች በበዛ ለማፍ ችሎታ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ሌሎች ተለውጦዎች

እንደሚኖሩ ያሚለክታል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ያልተዳሰሱ ሌሎች የማፍ ክሂል ተፅእኖ አሳዳሪ ተላውጦዎችን ያካተተ ተጨማሪ ጥናት ቢደረግና ከክሂሉ ችሎታ ጋር ያላቸው ዝምድና ቢታወቅ፣

2. በቁጥር አንድ ከቀረቡት ነፃ ተላውጦዎች መካከል ከተማሪዎች የማፍ ችሎታ ጋር የበለጠ አዎንታዊ ዝምድና ያለው የክፍል ደረጃ ሲሆን፣ የበለጠ አሉታዊ ዝምድና ያለው ደግሞ የትውልድ ቦታ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ከከተማ ልጆች ይልቅ የገጠር ልጆች የማፍ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡ ስለዚህ መምህራን የማፍ ክሂልን ሲያስተምሩ ለገጠር ልጆች የተለየ ትኩረት ቢሰጡየሚል ምክረ-ሃሳብ ያሰጣል፡፡

**ዋቢ ፅሁፎች**


ሚሩአለሙ፡ (1996)፡፡ *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡* አ.አ.፣ ብርሃንና ሰላምማተሚያ ድርጅት፡ ፡

ሚሩ አለሙ፡ (2003)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡* (፪ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚድርጅት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባየ ይማም:: (2000):: *የአማርኛ ሰዋስው(የተሻሻለ)፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.ሚሚሚድ

ሰለሞን ሀለፎም፡ (1989)፡፡ "አማርኛን በማስተማሪያ ዘዴነት የቃል ፅህፈት (Dictation) ሚና፡፡" ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተማ)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ:: (1986):: *አንብቦ የሚዳትና የማፍ ችሎታን ማዳበር፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.ሚሚሚድ

ጌታቸውቸርነት፡፡ (2001)፡፡ "በደብረ ማርቆስ ከተማየማ ኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የማፍ ክሂል ችሎታ ንፅፅራዊ ጥናት፡፡" (ያልታተመየሁለተኛ ዲግሪ መሟቂያ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ማርሀ ግብር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ፋንቱ ደምሴ፡፡ (1989)፡፡ "የፆታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመፃር ረገድ ያለውሚና፤ በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትየ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡" (ያልታተመየሁለተኛ ዲግሪ መሟቂያ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ማርሀ ግብር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

ያለውእንዳወቀ ማኅ:: (1998):: *የምርምር ማኅረታዊ ሚሆዎችና አተገባበር (ሁለተኛ እትም፡ ፡* ባህር ዳር፣ አብክመትምህርት ቢሮ፡ ፡

Abu Shawish, J. (2009). “Analysis and Assessment of Palestinian EFL Majors’ Written English”.Unpublished Ph. D. Thesis.Sudan University of Science and Technology.Cartum.

Adas, D. and Bakir, A. (2013). Writing Difficulties and New Solutions: Blended Learning as an Approach to Improve Writing Abilities. *International Journal of Humanities and Social Science,* 3 (9), 254-266.

Adeyemi, D.A. (2008). The Gender Factor in Composition Writing with the Use of the Cooperative and

Individualized Approaches at a Junior Secondary School in Botswana, *Journal of Educational Enquiry,* 8 (1), 1-9.

Bilal, H.A., and et al. (2013). Investigating the Problems Faced by the Teachers in in Developing English Writing Skills. *Asian Journal of Social Science and humanities,* 2( 3), 238-244.

Callahan ,F. J. and Clark, L. H. (1988). Teaching in the Middle and Secondary Schools: planning for competence. (Third Ed.), Macmillan publishing company.

Carpenter, P.C. & Lehrer, R. (1999).Teaching and Learning Mathematics with Understanding.In E. Fennema & Romberg, T. A. (Eds).*Mathematics classrooms that promote understanding.*London: Lawrence Erlbaum Associates Publishers.

Chase, B.J. (2011). “An Analysis of the Argumentative Writing Skills of Academically Underprepared College Students” Unpublished Doctor of Philosophy Thesis, Columbia University, Columbia.

Chokwe, M.J. (2011). “Academic English in Writing in English Second Language Contexts: erceptions and Experiences of First Year University Students and Tutors.” Unpublished Degree of Master, Specialization in TESOL,University of South Africa.

Cliff, A. and Hanslo, M. (2009).The design and use of alternate assessments of academic literacy as selection mechanisms in higher education. *Southern African Linguistics and Applied Language Studies*, 27(3), 265-276.

Clouthier, G. & Shandola, D. (1993). Teacher As Researcher. In Owens, D.T. (ed). *Research Ideas for the Classroom: Middle Grades Mathematics.* New York: Macmillan Publishing Company.

Collier, Virginia P. (1988). “The Effect of Age on Acquisition of a second Language for School” George Mason University.

Creswell, J.W. (2012). *Educational Research: Planning, Conducting and Evaluating Qualitative and Quantitative Research*. Boston: Pearson Education Inc.

Cumming, A. (2003). Experienced ESL/EFL writing instructors’ conceptualizations of their teaching: Curriculum options and implications. In B. Kroll (Ed.), Exploring the dynamics of second language writing (pp. 71-92). Cambridge, UK: Cambridge University Press.

Dorneyei, Z. (2007). Attitudes orientations and Motivation in Language Learning.Advances in theory,Research and Applications Language Learning.*A Jornal of research in language studies.*V.53, pp 3-32.

Elashri, I.I. (2013). “The Effect of the Gener-Based Approach to Teaching Writing on the EFL AL-Azher Secondary Students’ Writing Skills and Their Attitudes towards Writing.” Unpublished Phd Dissertation, Faculty of Education, Department of Methods and Curriculum, Mansoura University, Mansoura.

Finlay, L. (2004 April).Where the Boys are.*Todays’ Parent*, 21(3), 65-68.

Fisher, R. (2012). Teaching Writing: a Situated Dynamic. *British Educational Research Journal*, 38(2), 299 - 317.

Fisher, R., Michill, D. and Twist, L. (2011).Evaluation of Every Child a writer Report 2. Teaching and Writing in EC2W Classes. University of Exeter and National Foundation for Educational Research. DfE RR1086.

Farooq, M.S., Uzair-Ui-Hassan, M., Wahid, S. (2012).Opinion of Second Language Learners about Writing Dificulties in English Language.*A Research Journal of South Asian Studies,* 27(1), 183-194.

Gomathi, B. S. (2014). “Enriching the skills of Rural Students with Effective Methods of teaching English language using LSWR skills.*International Journal of Education and Information Studies.* 4(2), 65-69.

Granville, S. and Dison, L. (2009).Making connections through reflection: writing and feedback in an academic literacy programme.*Southern African Linguistics and Applied Language Studies,* 27(1), 53-63.

Harmer, J. (2001).*The Practice of English Languege Teaching.*London: Prentice Hall international.(UK) Ltd.

Hirst, E, Henderson, R, Alan, M, Bode, J and Kocatepe. (2004). Repositioning academic literacy: Charting the emergence of a community of practice. *Australian Journal of Language and Literacy*, 27(1), 66-80.

Hughes, A. (1989). *Testing for Language Teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Hurlock, E., B. (1972). *Child Development*. New York: MacGraw. Hill Book Company.

Hutchinson, T. and Waters, A. (1987).*English for Speecific purposes: A Learning Centred Approach.* Cambridge: Cambridge University Press.

Hyland, K. (2003). *Second Language Writing.* Hong Kong: Cambridge University Press.

Javed, M., Juan, W.X. and Nazli, S. (2013). A Study of Students' Achievement in Writing Skills of the English Laguage. International Journal of Instruction, 6(2), 129-144.

Kilpatrick, W.H. (1985). *Foundations of Method*. New York: Macmillan.

Lea, M.R. and Street, B.V. (1998). Student Writing in Higher Education: an academic literacies approach. *Studies in Higher Education,* 23(2), 157-172.

Lydia, Muthoni kamau. (2013). "Relation ship between family back ground and Academic Performance of Secondary School Students": A case of Siakago Division,Mbeebre Notrh District,Kenya.

Marczyk, G., Dematteo, D. & Festinger, D. (2005).*Essentials of Research Design and Methodology.* USA: John Wiley & Sons,Inc.

McGroarty, Mary (2009) " Language attitude,Motivation, and Standards." In Mckay, Sandra Lee and Hornberger,Nancy H. (2009) *Sociolinguistics and Language Teaching.* USA: Cambridge University Press.

Mochesela, P.R. (2007). "The Role of the Problem Based Approach In the Performance of Grade 9 Learners In Solving Word Problems." Unpublished Masters Paper, University of South Africa, Mathimatics Education, South Africa.

Moochi, C. N.,Isaac, M. B. and Ipara,P.O. (2013). Performance Differences and Gender in Kiswahili Creative Writing: A Case Study of Selected Secondary Schools in Nyamira County, Kenya, *In the Journal of Pan African Studies*, 6(1), 37-52.

Moore, R. (1998). How science educators construe student writing. In Angelil-Carter, S. (Ed.) *Access to success: Literacy in academic contexts*. Cape Town: University of Cape Town Press.

Muijs, D. (2004). *Doing Quantitative Research in Education with SPSS.* London: Sage Publications

Munro, J. (2003). Fostering Literacy across the Curriculum.*International Journal of Learning*, 10(1), 327-336.

Myhill, D. and Fisher, R. (2010 eds.). Writing Development: Cognitive, Socio cultural, Linguistic Perspectives. *Journal of Research in Reading*, 33(1), 35-44.

Nacira, G. (2010). "Identification and Analysis of Some Factors' Poor Writing Productions: The Case Study of 3rd Year Students at the English Department – Batna University." Unpublished Phd Dissertation, University of Setif, Faculti of Letters and Social Sciences, Department of Social Sciences, Setif.

Niven, P.M. (2005). Exploring first year students‟ and their lecturers‟ constructions of what it means to read in the humanities discipline: a conflict 162 of frames? *South African Journal of Higher Education*, 19(4), 777-789.

Nunan, D. (1989). *Designing Tasks for the Communicative Classroom*. Cambridge: CUP.

Patrick, N.L. (2009). The Power of Problem Based Learning (PBL) in the EFL Classroom. *Polglossia,* 16(1) 41-48.

Pintrich, R. and Shunk, H. (2002).*Motivation in Education theory.* New York: Cambridge university press

Richards, J. C., & Renandya, W. A**.** (2003).*Methodology in language teaching:An anthology of current practice.* (3rd ed.).Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. & Rodgers, T.S. (2001).*Approaches and methods in language teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Richardson, V. (2003).Constructivist pedagogy.*Teachers College Record*, 105(9), 1623-1640.

Robinson, P. (2001). *Cognition and 2nd language instruction*. U.N: Cambridge University press.

Robson, C. (1993). *Real World Research: A Resource for Social Scientists and Practitioner Researchers (2nd Ed.).* UK: Blackwell Publishing.

Rogers, C.G., Galloway, D., Armstrong, D. and Leo, E. (2000).Gender Differences in Motivational Styles.*European Education*, 32(4), 79-99.

Russell, D.R. (2002). *Writing in the academic disciplines: A curricular history*. Carbondale, IL: Southern Illinois University Press.

Sage, S.M. (2000). A Natural Fit: Problem-based Learning and Technology Standards. *Learning & Leading with Technology*, 28(1), 6-17.

Savery, J.R. (2006). Overview of problem-based learning: Definitions and distinctions. *The Interdisciplinary Journal of Problem-based Learning*, 1(1), 9-20.

Savery, J.R., & Duffy, T.M. (1995). Problem Based Learning: An Instructional Model and Its Constructivist Framework. *Educational Technology*, 35(5), 31-38.

Savery, J. R., & Duffy, T. M. (2001).*Problem-based learning: An instructional model and its constructivist framework (Tech. Rep. No. 16-01)*. Bloomington: Indiana University, Center for Research on Learning and Technology.

Savin-Baden, M., & Major, C.H. (2004).*Foundations of problem-based learning*. New York: Open University Press.

Shwartz, S. (2004). Should young people delay college? A Modest Proposal.*Phi Kappa Phi FORUM*, 84(4), 37-48.

Silva, T. (1990). Second language writing: Research insights for the classroom. In B. Kroll (Ed.), *Second language composition instruction: developments, issues, and directions in ESL* (pp.11-23). Cambridge: Cambridge University Press.

Silva, T. (1993). Toward an Understanding of Distinct Nature of L2 Writing: The ESL Researc and its Implementations. *TESOL Quarterly*, 27(4), 657-675.

Silver, EA.; Kilpatrick, J.& Schlesinger, B. (1990). *Thinking Through Mathematics: Fostering Inquiry And Communication In Mathematics Classrooms*. USA: College Board Publications.

Singh, Y. K. (2006). *Fundamentals of Research Methodology and Statistics*. New Delhi: New Age International Publishers.

Skinner, E. C. (1985). *Educational psychology*. ($4^{th}$ed). New York: prentice. Hall.Inc.

Solvberg, A.M. (2003). Computer-Related Control Beliefes and Motivation: A Panel Study. *Journal of Research on Technology in Education*, 34(4,), 473-487.

Spencer, B. (2007). Towards greater equality: Power and role relations involved in response to student writing. *Language Matters: Studies in the Languages of Africa*, 38(2), 299-315.

Styati, E.W. (2010). “The Effectiveness of Clustering Technique to Teach Writing Skill Viewed from Students Linguistic Intelligence” Unpublished Masters Thesis, Sebelas Maret University Graduate School English Education Department, Sebelas Maret.

Tudor, L. (1986). *Learner cemeredness as language Education*.New York. Cambride university press.

Weir, C. (1990). *Communicative Language Testing.* London: Prentice-Hall International (UK) Ltd.

Zhu, W. (2004). Faculty views on the importance of writing, the nature of academic writing and teaching and responding to writing in the discipline. *Journal of Second Language Writing*,13(1), 29-48.